# ይድረስ ለብርቱዋ! (ቁጥር 3)

ከከበቡሽ አያናቸው

ብረቱዬ ብረቱዋ ዛሬስ እንደምን ነሽ?
ይኸው ሳናስበው አንድ ወር አለፈሽ!
    ቀኑ እንዴት ይሮጣል? ይላል የተመቸው፣
    ላንቺ እያንዳንዱ ቀን ምን እንደሁ ሳያውቀው።
ብርቱዬ እንዴት አለሽ የትግል አርማችን፣
የድፍረት፣ የጽናት፣ የአንድነት ፋናችን፣
    ይቅርታ ብርቱዬ ትንሽ ሰንበት አልሁኝ፣
    በስንፍና ሳይሆን እንዲያው ግራ ገብቶኝ፣
    የማደርገው ጠፍቶኝ ጭንቅ ጥብብ ብሎኝ።
    ከውስጥም ከውጭም ያለው ተቀርቋሪ፣
    ድምጹን ከፍ አድርጎ ሲያደንቅ ያንችን ሱሪ፣
    እኔም ባለሁበት አምላኬን ለምኜ፣
    ይፈቱሽ ይሆናል ብዬ ተማምኜ፣
    ለእንኳንስ ደስ ያለን ብዕሬን ሳሰላ፣
    እኔ የማስበው የሚሆነው ሌላ።
የአረመኔዎቹን የመርገም በረከት፣
የነብርሃነን ሕገወጥ ሙግት፣
በየኢንተርኔቱ ስሰማው ሳነበበው፣
ዘመኑ ከፋና ልቤን አሳመመው።
    በወሬ በዝና እስከማውቀው ድረስ፣
    እናት፣ እህት፣ ልጆች፣ ሚስትም አለው መለስ፣
    ጭብጡን እያወቀው የዕርቃችሁን መንፈስ፣
    እንደምን ጨከነ እስከዛሬ ድረስ?
    ይገርማል ይደንቃል፣ አያድርስ! አያድርስ!
    ከቶ መስሎት ይሆን ዘላለም የሚነግሥ?
    አይዞሽ ቀን ይወጣል አምላክ ያለው ሲደርስ።
በስንት መጨጨህ በስንት ንዝነዛ፣
ጠበቃ መግባቱን ሰማሁ እንደዋዛ፣
የእግዜር ዳኝነት ነው ሁሉን የሚገዛ።
ብርቱዬ እህትዓለም በዓላማ ጽናትሽ፣
ደህና መሆንሽን ነገሩን ጠበቃሽ።
ከዚያ ጉሮኖ ውስጥ ሌት ተቀን ታጉረሽ፣
መከሳቱ መጥቆሩ እንደምን ይነስሽ?!
ሙቀት ቅዝቃዜው ሲፈራረቅብሽ?!
አይዞሽ ሁሉም ያልፋል ጠንክሪ በእምነትሽ።
ብርቱዬ ወሬውን ሰምተሽው ይሆናል፣
እኔም ያየሁትን ልንገርሽ በእኔው ቃል።
    በምዕራብ በኩል አንድ ኮከብ ታይቷል፣
    ብርቱዬ! ደግ ቀን ይወጣ ይሆናል።
    ሲሸጥ፣ ሲቀጠቀጥ፣ ለነበረው ሁሉ፣
    ብርሃን ፈነጠቀ አበራ ጸዳሉ፣
    በነጭ አደባባይ ታየ በአካሉ፣



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ለማመን አቃተው ዓለምን በሙሉ።
ይኸ የአጥቢያ ኮከብ ብዙ ስም ሞልቶታል፣
ከእግዜር የተላከ ብሩክም ይሉታል፣
ያለም ሕዝብ በሙሉ ተሥፋ ጥሎበታል።
ብርቱዬ ይገርማል የዚህ ሰው ስጦታ፣
እጥፍ ድርብርብ ነው፣ በመንታ በመንታ፣
እያሰበ ይናገራል፣
እየተናገረ ያስባል፣
ራዕዩን በአእምሮው ይጽፋል፣
በአእምሮውም ያነባል።
በዓላማው ጽናት የኮራ፣
በመጽሐፉ እንዳለው፣
"የተስፋ ጥንካሬ"
(The Audacity of Hope) ያለው፣
የእግዜር መደነቂያ ፍጥረት ነው።
ለ18 ደቂቃዎች
ዕቅዱን በቃል ሲዘረዝር፣
ከእጁ ማስታዎሻ የለውም፣
ከአዕምሮው በስተቀር።
"ይቻላል" ያለው ተችሏል፣
ለማንኛውም ክፍለ-ዓለም፣
የሰላም እጁን ዘርግቷል፡
በተሳሳተ መንገድ ያሉትንም፣
አንባገነኖች በሙሉ፣
መንገዳቸውን እንዲያቀኑ፣
ጠርቷቸዋል በቃሉ።
መንገዱን ለሳተና አሻፈረኝ ለሚል፣
አሜሪካ ደካማ እንዳልሆነች ያለማወላዎል አረጋግጧል።
እንደሀገራችን ሰባኪ መለኩሴ፣
አጣምሮ እንደያዘው አንከሴ፣ (መስቀል ተሰላጢን)
ኦባማም ሲያስተምር እንደሳቸው ብሏል።
በሰላም የመጣ በዚህ ይባረካል፣
በሐኬት ከመጣም በአንካሴው ይወጋል፡
ምርጫው የራሱ ነው በማለት አውጇል።
ብርቱዬ የዚህ ሰው ዕድገቱ ትምህርቱ፣
በጽናት ያገኘው የሥራ ብቃቱ፣
በነጩም በጥቁሩም አስብሎታል አንቱ።
ያንችም ኦባማነት አይቀርም በከንቱ።
የቃል ኪዳኑ ዕለት ያየሁትን ትንግርት፣
ልነግርሽ አልችልም ይፈልጋል ትዕግሥት።
*በአጭሩ፡* ጥቁር አሜሪካዊ መሪ ሆኖ ተመረጠ፤
ካፒቶል ሂል መዲናቸው አንበሳው ሲያገሳ ተናጠ፤
አደባባዩ በሙሉ ብሕዝብ ብዛት አበጠ፤
ኦባማን አቀነቀነ፣ የደስታ ፉጨት አፏጨ፤
ስሜቱ ፈነቀለው፣ ዕንባ በዕንባ ተራጨ።
"ይቻላል" ያለው ተቻለ፤


Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ዓለም በሙሉ ጉድ አለ።
ታዲያ ይሁን እንጅ አሁንም ኦባማ ለማዳው አንበሳ፣
ድምፁ በቁጣ ይሰማል፤ በተደጋጋሚ ሲያገሳ፣
የሚመጣውን አደጋ በማስረጃ እያነጠረ፣
በጀቱን ለማስፈቀድ ያለመሰልቸት ብዙ ጣረ።
የሕዝቡን ሙሉ ድጋፍ በአደባባይ ቢያገኝም፣
በሰኔት ያለው ትግል፣ ቀላል ሆኖ አልተገኘም።
ሪፐብሊካኖች በምርጫው ያጡትን የምርጫ ድል፣
በበጀቱ ለመወጣት እጅግ ብዙ ጥረዋል።
ግን ቢወድም ባይወድም በጀቱን አጽድቀዋል፤
ሕዝብ የመረጠውን የሕዘብ ልጅ ማን እምቢ ሊል ይችላል?
የሕዝብ የበላይነት አንቀጥቅጦ ይገዛል።
ኢኮኖሚውን በመታደግ ቃሉን ለመጠበቅ ቸኩሏል፤
ሌላውም በየተራ እንደተራው ይቀጥላል።
በርች የእኔ እመቤት ብርቱዬ የእኔ ዞግ፣
ለዚህ ያበቃ አምላክ ዓለምን ሊታደግ፣
የኦባማን ዕድል የኦባማን ፈለግ፣
በፍፁም አምናለሁ ለእኛም እንደማይነፍግ።
በአንባ ገነን ሥርዓት፣ በአንባገነን መሥመር፣
መታሠር መፈታት፣ መፈታት መታሠር፣
የታጋይ ሕይዎት ነው ምንጊዜም የማይቀር፣
የታሪክ አተላው ካፈረበት ይፈር።
በተንኮል ያሠሩሽ ሕሊና ካላቸው፣
ነግ በእኔ ማለትን እግዜር ያሳያቸው።
የታሪክ ሐቅ ነው ይደርሳል ተራቸው።
ብርቱዬ አሁንማ ሁሉም አልቆባቸው፣
የወያኔ ልጆች አዲሱ ስልታቸው፣
ስም መበከል ሆኗል በአይጋ ቱልቱላቸው (ፎረማቸው)
የወያኔ ልጆች በጣም ያስቃሉ፣
እነፐሮፌሰር መስፍንን ሲያጥላሉ፣
ይበልጥ ተጋለጡ ትዝብት ላይ ዋሉ።
ተባረቃባቸው የሚሉቱ ሁሉ።
ብርቱዬ ይታያል ቀኑ መቃረቡ፤
ወገንሽ በሙሉ ካንች ጋር ነው ልቡ፣
ምንም አይቀናቸው እነግፍ ቀለቡ።
ትግሉ ተጠናክሯል፣ ሕዝቡ ተነሳስቷል፣
ለእኔ እንደሚታየኝ ደግ ቀን ይወጣል፣
የምታምኚው አምላክ አምላካችን ያውቃል።

ቸር ያሰማን
የምሳሳልሽ ከበቡሽ ነኝ።


Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com